ትምህርታችሁን በውጤት ምክንያት አቋርጣችሁ/Withdrawal/ ዳግም ቅበላ /Readmission/ ከተሰጣችሁ “C-“፣ “D” እና “F” ያመጣችሁባቸውን ኮርሶች ብቻ እንደገና ትመዘገባላችሁ።

4. **<u>Add እና Drop /ኮርስ መጨመርና መቀነስ/</u>**

ባለፉ ሴሚስተሮች  “F” ያመጣችሁባቸውን ኮርሶች አሁን ባላችሁበት ሴሚስተር ካሉ ኮርሶች ላይ ጨምራችሁ (Add) መውሰድ ትችላላችሁ። “F” ባመጣችሁት ኮርስ ምክንያት በአሁኑ ሴሚስተር የማትወስዱት ኮርስ ካለ ይቀነሳል(Drop):: ወይም ጨምራችሁ በምትወስዱት ኮርስ ምክንያት በሴሚስተር መውሰድ ከሚፈቀደው ክሬዲት ፖይንት በላይ የሚሆን ከሆነ፣ ከ አድቫይዘራችሁ ጋር ተማክራችሁ የምትቀንሱት (Drop) ኮርስ ይኖራል።